የ 2016 ዓ.ም. የመጀመሪያው መንፈቅ ዓመት የአምስተኛ ክፍል የሒሳብ መለማመጃ ጥያቄዎች

መመሪያ ፩፦ የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ "ሀሰት" በማለት በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ፃፉ።

_____1) አራቱም ጎኖቹ እኩል የሆነ የጎነ-አራት ምስል ሬክታንግል ይባላል።

_____ 2) 1 ሄክታር = 10,000 ሜ^2 ነው።

_____ 3) ማንኛውም ነገር ሊይዘው የሚችለው ቦታ ልኬት ይዘት ይባላል።

_____ 4) አንድ ኩብ ርዝመቱ 3 ሳ.ሜ ቢሆን የኩቡ ይዘት 27 ሳ.ሜ^3 ነው።

_____ 5) የይዘት ልኬት የሚገለፀው ካሬ ምድብ ነው።

መመሪያ ፪፦ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛው መልስ የያዘውን ፊደል መርጣችሁ በመልስ መስጫ ቦታው ላይ ፃፉ።

_____6) 3 ሳ.ሜ.^{3} ስንት ሚ.ሜ^2 ነው?

ሀ. 30 ሚ.ሜ^3 ለ. 300 ሚ.ሜ^3 ሐ. 100 ሚ.ሜ^3 መ. 3,000 ሚ.ሜ^3

_____7) 8 ሊ. ወደ ሳ.ሜ^3 ሲቀየር ስንት ይሆናል?

ሀ. 8,000,000 ሳ.ሜ^3 ለ. 80,000 ሳ.ሜ^3 ሐ. 8,000 ሳ.ሜ^3 መ. 800 ሳ.ሜ^3

_____8) የጎኖቹ ርዝመት 6 ሳ.ሜ ያለው ካርቶን ስንት ባለአንድ ሳ.ሜ^2 ስፋት ያላቸው ትንንሽ ካሬዎች ይኖሩታል?

ሀ. 18 ሳ.ሜ^2 ለ. 12 ሳ.ሜ^2 ሐ. 36 ሳ.ሜ^2 መ. 24 ሳ.ሜ

_____9) ርዝመቱ 8 ምድብ እና ወርዱ 5 ምድብ የሆነ ሬክታንግል ስፋት ስንት ነው?

ሀ. 40 ካሬ ምድብ ለ. 26 ካሬ ምድብ ሐ. 13 ካሬ ምድብ መ. 64 ካሬ ምድብ

_____10) የአንድ ኩብ ርዝመት 8 ሳ.ሜ ቢሆን የኩቡ ይዘት ስንት ነው?

ሀ. 64 ሳ.ሜ^3 ለ. 512 ሳ.ሜ^3 ሐ. 512 ሳ.ሜ^2 መ. 64 ሳ.ሜ^2

መመሪያ ፫፦ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ።

11) ለሚከተሉት ምስሎች ይዘታቸውን ፈልጉ።

ሀ)



ለ)



12) የሚከተሉትን የይዘት ምድቦች ወደ ተጠቀሰው የይዘት ምድቦች ቀይሩ።

ሀ) 8 ሳ.ሜ^3 ወደ ሚ.ሜ^3

ለ) 8,240,000 ሳ.ሜ^3 ወደ ሜ^3

13) የአንድ ት/ቤት የእግር ኳስ ሜዳ 30 ሜ በ 30 ሜ ነው። የእግር ኳስ ሜዳው ስፋት ስንት ይሆናል?